# የትምህርት ዘርፉን ገድሎ ማልቀሱ ይቁም!

የኢህአዴግ አመራር በሥልጣን ዘመኑ ያስመዘገባቸው ድሎችን ሲዘረዝር በቅድሚያ የሚያቀርበው በትምህርት ዘርፍ የተገኘውን ድል ነው፡፡ ያለፉት መንግሥታት በመቶ ዓመታት ያላስመዘገቡትን ድል በአጭር ጊዜ እንዳስመዘገበ በአፅንኦት ይናገራል፡፡ ለዚህ በአብነት ተጠቃሽ የሚያደርገውም በደርግ ዘመን መጨረሻ ከ21% በታች የነበረውን የመጀመሪያ ደረጃ አጠቃላይ የትምህርት ሽፋን በአሁኑ ጊዜ 100% ገደማ መድረሱን ነው፡፡ በእርግጥ በአገራችን አጠቃላይ የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ሽፋኑ 100% አካባቢ ደርሷል፡፡ የሁለተኛ ደረጃና የዩንቨርስቲ ትምህርቶችም ከአሃዝ አንፃር ከፍተኛ እምርታ አሳይተዋል፡፡

በእርግጥ ባለንበት ዘመን ሁሉም በዓለማችን ያሉ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እንደ መብት ማግኘት አለባቸው የሚል «በሚሊኒየም የልማት ግብ» ስም የታወጀ መርሃ ግብር ስላለ ማንኛውም በማደግ ላይ ያለ አገር ይህን ግብ እንዲያሳካ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ ይህን ግብ ለማሳካት የሚጥር አገር ከምዕራባውያን ለጋሾች ዕርዳታ ሲያገኝ ግቡን ያላሳካ ደግሞ ዕርዳታ ይቀነስበታል፡፡ በመሆኑም በትምህርት ዘርፍ የተቀመጠውን ግብ ማሳካ መንግሥታት የሚያሳዩት ቁርጠኝነት ውጤት ሳይሆን የለጋሾች አስገዳጅነትና የዕርዳታ ማትግያ ግፊት የወለደው ነው፡፡ የኢህአዴግ መንግሥትም ከለጋሾችና ከዓለም ዓቀፍ ተቋማት ጋር ይህን ውለታ ስለገባ ከፍተኛ ዕርዳታ እየተለገሰለት የትምህርት ዘርፍ ግቦችን ለማሳካት እየጣረ ይገኛል፡፡

የተለያዩ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ከአሃዝ አንጻር የተቀመጡላቸውን ግቦች በማሳካት ላይ እንደሆኑ ቢታወቅም ዘርፉ በከፍተኛ ችግሮች ተተብትቦ ቀውስ ውስጥ መዘፈቁ ግን አሌ የማይባል ነው፡፡ የአገራችን የትምህርት ዘርፍም እንዲሁ ቀውስ ውስጥ ተዘፍቆ ይገኛል፡፡ መንግሥት በትምህርት ረገድ በትክክል ግዴታውን ተወጥቷል ሊባል የሚቻለውም እነዚህ ለቀውስ የዳረጉ ችግሮችን መፍታት ሲችል ነው፡፡ ሆኖም ለዓመታት በትምህርት ዘርፍ የሚታዩትን ችግሮች መፍታት ቀርቶ መሠረታዊ ችግሮች እንኳ በውል ሊታወቁ አልቻሉም፡፡ ችግሮች በአግባቡ ባልተወቁበት ሁኔታ በርካታ የመፍትሄ ሐሳቦች ቢደረደሩም በዘርፉ የተከሰተውን ቀውስ ሊፈቱ አይችሉም፡፡ ችግሩን

ከመሠረቱ ለማየት ያልቻለው ኢህአዴግ አንዴ መምህራንን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ተማሪዎችን፣ ሲያሰኘው ደግሞ ኅብረተሰቡን ተጠያቂ እያደረገ ነው። ለመሆኑ የአገራችን የትምህርት ችግሮች መሠረታዊ መንስኤዎቻቸው የትኞቹ ናቸው??

## 1. <u>የትምህርት ፍልስፍናና ፖሊሲ ችግሮች</u>

በርካታ የትምህርት ዘርፍ ባለሙያዎች እንደሚሉት ከሆነ አንድ መንግሥት ስለ ትምህርት ጥራት፣ ብቃትና ቅልጥፍና ከማወሳቱ በፊት መጀመሪያ ማንሣት ያለበት ትምህርቱ የሚመራበትን ፍልስፍና የተመለከተ ነው። ትምህርት የሚመራበት ፍልስፍና ትክክል ከሆነ ሌሎች ዝርዝር ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ሊስተካከሉ ይችላሉ፤ ፍልስፍናው የተሳሳተ ከሆነ ግን ፖሊሲዎችና መመሪያዎችም የተሳሳቱ ይሆናሉ። በመሆኑም የአንድ አገር ትምህርት የሚመራበት ፍልስፍና በአጠቃላይ የትምህርት ሁኔታው ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖረዋል። ከዚህ አንፃር ሲታይ የአገራችንን ትምህርት የሚመራው ፍልስፍና በውል የታወጀ ባይሆንም እንደሌላው ዘርፍ ሁሉ የኢህአዴግ «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» ማኅተም እንዳረፈበት ግልፅ ነው። የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በሁሉም የኅብረተሰብ የእንቅስቃሴ ዘርፎች የበላይነት መቀዳጀት አለበት ስለተባለ በትምህርቱ ዘርፍም የበላይነት እንዲቀዳጅ ጥረት እየተደረገ ይገኛል። መላ የአገሪቱ መምህራን «አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ ዴሞክራሲና ልማት» የሚለውን ንፋፊ ጽድቅ እንዲወያዩ እየተደረገ ያለውም ይህን ፍልስፍና ለማስጨበጥና መመሪያቸው አድርገው እንዲሠሩበት ነው። ይህ ማለት በትምህርት ዘርፉ የኢህአዴግ የበላይነትና የቁጥጥር የፖለቲካ ፍልስፍና ገዢ መመሪያ ሆኖ ይቀጥላል ማለት ነው።
የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ፍልስፍና የበላይነት በተቀዳጀበት ሁኔታ ደግሞ በትምህርቱ ዓለም «ነፃነት፣ እኩልነትና አገር ወዳድነት» ደብዛቸው ይጠፋል ማለት ነው። ለምን ቢሉ እነዚህ የፍልስፍና መሠረቶች ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋር የሚጣጣሙ አይደሉምና። ነፃነት የትምህርት ፍልስፍና አንድ መሠረት ተደርጎ በማይታይበት ሁኔታ የአካዳሚ ነፃነት ኖሮ ምርምር፣ ፈጠራና ተነሳሽነት ሊዳብር አይቻልም። ባለፉት ዓመታት የአገራችን ሙሁራን የአካዳሚ ነፃነት ይኑር የሚል መፈክር በማሰማት ተደጋጋሚ ትግል ያካሄዱት ለዘርፉ ዕድገት ያለውን ጠቀሜታ ታሳቢ በማድረግ ነበር። ሆኖም አስተሳሰቡ ነፃነትን ከሚፃረረው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋር ሊጣጣም ባለመቻሉ ተዳፍኖ እንዲቀር ተደርጓል። የትምህርት ጥራት፣ ብቃትና ቅልጥፍና ጥያቄ የትምህርት ፍልስፍና አንዱ መሠረት ከሆነው የአካዳሚ ነፃነት ተለይቶ ስለማይታይ ልዩ ትኩረት ማግኘት ይኖርበታል።

አብዮታዊ ዴሞክራሲ የትምህርት ፍልስፍና መመሪያ ተደርጎ በተወሰደበት ሁኔታ ፍትህና እኩልነትም ሊኖር አይችልም፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወገንተኝነትን መሠረት ያደርጋል፡፡ በመሆኑም አብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የማይቀበልና በዚህ አስተሳሰብ የሚመራው ፓርቲ አባልና ደጋፊ ያልሆነ ወገን በትምህርት ዘርፉ ቦታ አይኖረውም፡፡ የዘርፉ ዋና መሪና ተጠቃሚ ይህን ፖለቲካ አራምዳለሁ የሚለው ወገን ነው፡፡ ሙያና ብቃት ባይኖሮውም በአብየታዊ ዴሞክራሲ ያምናል እስከተባለ ድረስ ይህን የሚልዮኖችን ሕይወት የሚነካውና እጅግ ውድ የሆነውን ትምህርት እንዲመራ ይደረጋል፡፡ ለአገራችን የትምህርት ውድቀትና ዝቅጠት አንዱ ምክንያትም ሙያና ብቃት የፍትሕና እኩልነት መመዘኛ መስፈርቶች መሆናቸው ቀርቶ በፖለቲካ ወገንተኝነት መተካታቸው ነው፡፡

ሌላው የትምህርት ፍልስፍና መሠረት አገር ወዳድነትን ማዳበር መሆን ሲኖርበት በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ  ቦታ የማይሰጠው ሆኗል፡፡ በህዝቡ ግፊትና ተቃውሞ ምክንያት ኢትዮጵያዊነትና አገር ወዳድነት በመፈክር ደረጃ አልፎ አልፎ ቢወሳም የአገሪቱ የትምህርት ፍልስፍና እንድ ምሰሶ ሆኖ በሥርዓተ ትምህርቱና በአጠቃላይ አስተሳሰቡ የተቀረፀ አይደለም፡፡ እንዲያውም ኢህአዴግ በዘበነ ግሎቫላይዘሽን አገር ወዳድነት የሚለው ፅንሰ ሃሳብ የኋላ ቀሩና ያልሰለጠነው ፋራ አስተሳሰብ አድርጎ የሚወሰድበት ሁኔታ ይንፀባረቃል፡፡ ለኢህአዴግ ከዘላቂው የአገር ጥቅም ይልቅ በስመ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚያራምደው የአገዛዝ የበላይነትና የሥልጣን መደላደል ይቀድማል ፡፡ ሆኖም አገር ወዳድነት በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ በሚገባ ካልተቀረፀ ወጣቱ ትውልድ ወዴት አቅጣጫ እንደሚሄድ ጠፍቶት የተደናበረ ሆኖ ይቀራል፡፡ በአገራችን የትምህርት ጥራት፣ ቅልጥፍናና ውጤታማነት ሲነሳም ከዚህ ፍልስፍና ጋር ትስስር ያለው ነው፡፡

ከትምህርት ፍልስፍናው ጋር አብሮ  የሚነሳው ጉዳይ የትምህርት ፖሊሲ ነው፡፡ ፖሊሲ በአብዛኛው ከፍልስፍናው የሚመነጭ ነው፡፡ ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው የፍልስፍናው መሠረት አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሲሆን ፍልስፍናው በአስተማሪው፣ በተማሪውና በአጠቃላይ ኅብረተሰቡ እንዲቀረፅ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ ይህን ጥረት ለማስፈፀም የሚያስችሉ በርካታ ፖሊሲዎችም ተግባራዊ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው፡፡ በትምህርት ዘርፉ ጐልተው ከሚታዩት የኢህአዴግ ፖሊሲዎች መካከል ከሙያና ብቃት ይልቅ ለፖለቲካ ታማኝነት ቅድሚያ መስጠቱ፣ ከዝቅተኛው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጀምሮ እስከ ዩንቨርስቲ ባሉት ተቋማት መሪ ለመሆን ለኢህአዴግ አባል ቅድሚያ መስጠቱ፣ ለተቋማት መሪነት ምልመላና ዕድገት በፓርቲ መዋቅሮች አማካይነት እንዲሆን መደረጉ፣ ትምህርት ቤቶች የፕሮፓጋንዳ ማዕከል እንደሆኑ መደረጋቸው ተጠ ቃሾች ናቸው፡፡

ትምህርት ቤቶች የአካዳሚና የምርምር ተቋማት መሆናቸው ቀርቶ በፓርቲ መዋቅር እንዲመሩና የፕሮፖጋንዳ ማእከላት እንዲሆኑ እየተደረጉ ለመሆኑ በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይችላል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ኢህአዴግ በቅርቡ ባወጣው የፕሮፓጋንዳ ሥራው

አቅጣጫ ቅድሚያ ሰጥቶ የሚንቀሳቀስባቸውን አካላት የትኞቹ መሆን እንዳለባቸው አማራጮችን ያስቀምጣል:: በበርካታ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት በአማራጭነት በማቅረብ የኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ ማሰራጪት የሚቻል መሆኑን ይገልፅና ከሁሉም አካላት ቅድሚያ ሰጥቶ መሥራት ያለበት ግን በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ወጣት ተማሪዎች በተሰማሩባቸው ትምህርት ቤቶች መሆን እንዳለበት አቅጣጫ ያሰቀምጣል:: እንደሚያስፈልግ ያትታል:: ኢህአዴግ ከሁሉም በላይ የሚጠነቀቅለት ስልጣኑን ማደላደል ስለሆነ ለትምህርት ልማት እምብዛም ደንታ ሳይሰጠው ትምህርት ቤቶችን የምልመላና የፕሮፓጋንዳ ማዕከል ለማድረግ በፕሮፓጋንዳ ፖሊሲው ቅድሚያ ሰጥቶ እንደሚሰራ አውጇል::

ከሁሉም በላይ የሚያስደነግጠውና የሚያሳዝነው የኢህአዴግ አ

አቅጣጫ ደግሞ ትምህርት ቤቶችን የፕሮፓጋንዳ ማዕከለ ከማድረግ አልፎ መምህራንና ተማሪዎች ተሸማቅቀው እንዲኖሩ የሚያደርግ ተጨማሪ አቅጣጫ መከተሉ ነው:: ለዚህ በአብነት አብነት ይሆነን ዘንድ ህወሓት የተማሪ ድርጅት አባላት መገምገሚያ ነጥብ በሚል ያሰራጨው መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ በትምህርት ቤት ያለውን ተማሪ አባል ለመገምገም ከተቀመጡት ነጥቦች  መካካልም

1ኛ/ አባሉ ተልእኮውን የሚያውቅ መሆኑ ማረጋገጥ

2ኛ/ በተማሪዎችና በመምህራን የሚነሱትን ችግሮች በምን ዓይነት መንገድ ይታገላል?

3ኛ/ ግዴታውን እንዴት ይወጣል? የድርጅት ጋዜጦችን ይወያያልን?

4ኛ/ አባላትን በመመልመል ረገድ ዕቅዶችን ይፈፅማልን?

5ኛ/ የጠላቶችን ሁኔታና እንቅስቃሴዎችን እንዴት ይከታተላል? የሚሉ ይገኙባቸዋል::

እንግዲህ እነዚህን መሰረት አድርጎ የሚንቀሳቀስ ተማሪ አባል ለትምህርት ጥራት አስተዋፅኦ ከማድረግ ይልቅ «የስለላ ተግባራትን» ለመፈፀም እየተዘጋጀ እንደሆነ ያመለክታል:: ኢህአዴግ ጠላት የሚላቸው ተቀናቃኝ ድርጅቶቹንና የፖለቲካ አቅጣጫውን የማይቀበሉ መሆናቸው ሲታሰብ ይህን አቅጣጫ ነድፎ የሚንቀሳቀሰው መዋቅር ብመማር ማስተማር ሂዴቱና በተማሪው ማህበረ ሰብ ላይ ምን ያህል ስጋትና ጥፋት ሊያስከትል እንደሚችል መገመቱ አያዳግትም::

ይህ ሁሉ ኢህአዴግ ወጣት ተማሪዎችን በአብዮታዊ ዴሞክራሲ በማስጥመቅ ቢያንስ ሊያነሱ የሚችሉትን ተቃውሞ ለማርገብ ከተሳካ ደግሞ ደጋፊዎቹ ለማድረግ አልሞ የቀረጸው ፖሊሲ ሲሆን አጠቃላዩን የትምህርት ቀውስ በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ ተጽእኖ ያለው ነው::

## 2. የትምህርት ዘርፉ ተቋማዊ ብቃት ማጣት

በአገራችን የትምህርት ዘርፍ ያለው ሌላው ትልቅ ችግር የትምህርት ሂደቱን የሚመሩ ብቁ ተቋማት ያለመኖራቸው ነው። እንደሌላው ሁሉ በትምህርት ዘርፉም የመሪነትና ቁጥጥር ወሳኝ ቦታ የያዘው ገዢው ፓርቲ ነው። ከገዢው ፓርቲ መካከልም ወናው ተዋናይ ያው ቁንጮው አቶ መለስ ናቸው። በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ መምህራን በቀጥታና በተዘዋዋሪ ሰብስበው ለሚነሱት ጥያቄዎች ሁሉ በእርግጠኝነት «መልስ» ይሰጣሉ። የሚመሩትን ፓርቲና ራሳቸውን ከተጠያቂነት ነፃ አውጥተው መምህራንን ተማሪዎችንና ኀብረተሰቡን ይዘልፋሉ። ጭራሽ ኅብረተሰቡን እንዳንቀላፋ አድርገው ይወቅሳሉ። እነዚህ የሚሰነዝሯቸው አስተያየቶች በየትኛው የትምህርት የምርምር ተቋም ተደግፈው የተጠኑ ናቸው? ቢባሉ መልስ የሚኖራቸው አይመስለኝም። ይህን የምልበት ምክንያት አለኝ። እስከሚገባኝ በአገራችን የሚታወቁ ነፃ የሆኑ የትምህርት የምርምር ተቋማት የሉም። በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች እንዲሠለጥኑ በተሰማሩበትና ብዙ ቢልዮን ብሮች በሚፈሱበት ዘርፍ አንድ የሚታወቅና አስተማማኝ የምርምር ተቋም ያለመኖሩ የትምህርት ዘርፉ አንዱ ክፍተት ነው። ታዲያ በትምህርት ዘርፍ ቀርቶ በአጠቃላይ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ዘርፉ እንኳ አስተማማኝ የምርምር ማእከል በሌለበት የኢህአዴግ መሪዎች ብዙ ችግሮችንና መፍትሄዎችን ቢደረድሩ ሳይንሳዊነታቸው እንዴት ይረጋገጣል?? ለመቀርቡት ጥያቄዎች የሚሰጡት መፈተሄዎችስ እውነተኛ ለመሆናቸው በምን ይረጋገጣል? የነጻና ጠንካራ የምርምር ተቋም አስፈላጊነት የሚነሣው እዚህ ላይ ነው ።

በትምህርት ሂደት ሌላው ወሳኝ ተቋም መምህራን የሚሰለጥኑበት ተቋም ነው። በእርግጥ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ከዝቅተኛው የአንደኛ ደረጃ መምህራን ማሰዕጠኛ ማእከላት እስከ ዩንቨርስቲ ድረስ ተቋቁመዋል። ሆኖም እነዚህ ተቋማት ከፖለቲካ ወገንተኝነት ፀድተው ሙያና እውቀት ብቻ መሰረት አድርገው ይሠራሉን? ከነዚህ ተቋማት ተመርቀው ለወጡትስ ከፖለቲካ ወገንተኝነት በፀዳ አግባብ ድልድልና ዕድገት ይደረጋልን? ሌላው ቀርቶ ለዘመናት ሙያና ብቃት በመስፈርትነት ተወስዶ ይደለደል የነበረው የትምህርት ቤቶች የዳይሬክትርነት ሹመት እንኳ አሁን የፖለቲካ ሹመት እየሆነ አይደለምን? ዋናው መሥፈርት ፖለቲካ ታማኝነት ከሆነ ከፖለቲካ ተቋም የሚለየው የለም ማለት ነው ።

ከዚህ ሌላ የትምህርት ዘርፉን ተቋማዊ ይዘት እንዲኖረው የሚያደርጉት ቋሚ አሰራሮች እንዲኖሩ የግድ ይላል። የመምህራን እድገትና ዝውውር የሚመለከት ቋሚና ፍትሓዊ አሰራር፣ ተማሪዎች የሚመዘኑበት ቋሚና አካዳሚያዊ አሰራር፣ የትምህርት እርከኖች ምክንያታዊ (rational) አቀራረጽ፣ የትምህርት ድጋፍ ሰጪ አካላት ሙያንና ችሎታን መሠረት ያደረገ አወቃቀርና፣ ወዘተ. ወጥና ተቋማዊ መልክ መያዝ ይኖርበታል። ይህ

ካልሆነ ኢህአዴግ ወይም መሪዎቹ በባነኑና በተደናገጡ ቁጥር የሚቀያየርና ፖለቲካዊ ታማኝነት መሠረት ያደረገና ዘላቂ ያልሆነ አሠራር ነግሦ የትምህርት ሂዴቱ ዘወትር እንደታመሰ ይቀጥላል፡፡ ለዚህ ሲባልም ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጣልቃ ገብነት ነፃ የሆኑና በቅጡ የተደራጁ የትምህርት ተቋማት መኖራቸው የግድ ይላል፡፡ ከዚህ ውጭ ስለትምህርት ጥራት፣ ብቃት፣ ውጤታማነት ወዘተ. ቢነገር ፋይዳ አይኖረውም፡፡ የአገራችን ትምህርት ከቀውስ መውጣት ያቃተውም ይህ የግድ ተግባራዊ መሆን የነበረበት መሠረታዊ ተቋማዊ አሠራር በፓርቲ አሠራር በመተካቱ ነው፡፡

## 3. <u>የትምህርት ግብአቶች እጥረትና አግባብነት ማጣት</u>

በመማር ማስተማር ሂደት ግብአቶች ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በተለምዶ የትምህርት ግብአቶች የሚባሉት መፃህፍት፣ ቤተ መፃሕፍት፣ ቤተ ሙከራዎች፣ ሰርቶ ማሳያዎችና ሌሎች ቁሳቁሶች ናቸው፡፡ በርካታ ትምህርት ቤቶች እነዚህ ግብአቶች እንደሚያጥሯቸው በየጊዜው ይነገራል፡፡ በዝቅተኛ የትምህርት እርከኖች ቀርቶ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም የግብአቶች እጥረቶች እንዳሉና ተማሪዎች በቂ ልምምድ ሊያደርጉ እንደሚያዳግታቸው ይገልፃሉ፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂዴት በቂ የግብአት አቅርቦት በሌለበት ሁኔታ ስለትምህርት ዕድገት መናገር በየትምህርት ቤቱ የታጎረውን ተማሪ አሃዝ ብቻ መግለጽ ይሆናል፡፡

ስለ ትምህርት ግብአቶች በተለይ ደግሞ ስለ መፃህፍት አቅርቦት ሲነሳ መታየት ያለበት አንድ ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም የሚቀርበው መጽሐፍ ይዘት ጉዳይ ነው፡፡ ብቃት ያለው ምርምር፣ የካሪኩለም ዝግጅትና የሰው ኃይል በሌለበት ተጽፈው የሚወጡ መፃህፍት የግብር ይውጣ እንጂ የተማሪውን አቅም የሚያጐለብቱ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ስለሆነም ግብአት ሲባል ተማሪውን በመቅረፅ ረገድ አግባብነት ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡

ግብአቶችን በማቅረብ ረገድ እንደ ችግር ሊወሰድ የሚችለው የገንዘብ እጦት ለሆን ይችላል፡፡ በእርግጥ በማንኛውም አገርና ሁኔታ የበጀት እጥረት ይከሰታል፡፡ እዚህ ላይ እየተነሣ ያለው አገራችን የምትችለውን የገንዘብ አቅርቦት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በተለይም በአገራችን ያለ አግባብ የሚባክነው የገንዘብ መጠን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ ለትምህርት ካላቸው ጠቀሜታ ይልቅ ለፖለቲካ ሥራና ለቁጥጥር ያላቸው ጠቀሜታ ገዝፎ የሚታየው «የፕላዝማ ቴሌቪዥኖች» ወጪ ለሌላ ግብአት ቢውል ኖሮ ምንኛ ውጤታማ በሆነ ነበር? ኢህአዴግ ለፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ብሎ የሚወጣው ገንዘብ ቢያንስ ግማሹ ለትምህርት ግብአቶች ቢውልስ በግብአት አቅርቦት ረገድ ምንኛ በጠቀመ

ነበር? በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የመንግሥት ሠራተኞች ለቀናት አልፎ አልፎም ለወራት ተቀምጠው ስለ አብዮታዊ ዴሞክራሲን ከሚወያዩ ይልቅ ወጪው ለትምህርት ግብአቶች ቢውልስ  ምንኛ ውጤታማ ሊሆን ይችል ነበር?

የትምህርት ግብአቶች ችግር ሲነሳ ጉዳዩ ከአቅርቦት ብቻ መታየት የለበትም ከብቃትና አግባብነት አንፃርም መታየት ይኖርበታል። ይህን በተመለከተ ሰሞኑን የአዲስ አበባ ዩንበርስቲ የድህረ ምረቃ ተማሪ በተሌቢዥን ቀርቦ ያለውን ማስታወሱ ተገቢ ይሆናል ።  ተማሪው በአንጋፋው የአዲስ አበባ ዩንበርሰቲ የኬኔዲ ቤተ መጻሕፍት ያለውን  የመጻሕፍቱ ዓቅርቦትና ዓይነት ሲገልጽ፣ መጻሕፍት እንደልብ ካለመገኘታቸው በተጨማሪ ያሉት መጻሕፍት በስድሳዎቹና በሰባዎቹ የነበሩ ናቸው ይላል ። በመሆኑም ተማሪዎች መጻሕፍት ቤቱን ቤት መጻሕፍት ከሚባል የመጻሕፍት ቤተ መዘክር ወይም ሙዝየሚ ቢባል ይሻላል ብለው እንደሚናገሩ ገልጿል ። ሁኔታው ይህ ሆኖ ሳለ ለተማሪዎች በነብስ ወከፍ መፃሕፍት ተዳርሷል ብሎ ከህዝብ ፊት መናገር የችግሩን ጥልቀትና ስፋት ከማድበስበስ ባሻገር ንቀትም ይሆናል።

## 4. <u>የተማሪዎች ሥነ ምግባር ችግር</u>

ከሁሉም በላይ የተማሪዎች ስነ-ምግባር ተበላሽቷል በማለት ኢህአዴግ የአዞ እንባ ሲያነባ የሚገርም ይሆናል። በዚህ ችግር ዙሪያ አቶ መለስ ሲናገሩ ችግሩ እንዲሁ ስር የሰደደው ብዙሃኑ ስላንቀላፉ ነው ብለዋል። ህዝቡን ወይም የታችኛውን አመራር ተጠያቂ በማድረግ ራሱን ነፃ በማውጣት የተካነው የኢህአዴግ አመራር በተማሪዎች ለሚታየው የሥነ-ምግባር ችግርም ተመሳሳይ ድራማ ሰርቶበታል። ለመሆኑ በተማሪዎች ለሚታየው የሥነ-ምግባር ጉድለት ዋና ተጠያቂ መሆን ያለበት ማን ነው?

እንደሚታወቀው የተማሪዎች ሥነ-ምግባር የሚቀረፀው በኅብረተሰብ፣ በመንግሥትና በአካባቢያቸው ባለው መልካም የሥነ ምግባር ተምሳሌትነት (Role Model) ነው። የተማሪዎች ሥነ-ምግባር የሚቀረፀው በዚህ አግባብ ከሆነስ ተማሪዎች ከመንግሥትና ከኅብረተሰቡ ምን እየተማሩ ነው። አሁን ባለንበት ሁኔታ ሙስና በአገራችን እጅጉን ተንሰራፍቷል። ሙስና ነውር መሆኑ ቀርቶ የጀግና ሥራ ተደርጎ ተወስዷል። ዘረፈ፣ መነተፈ የሚለው ቃል ራሱ «ቢዝነስ ሠራ» በሚል ተተክቷል። ይህ አመለካከትና አካሄድ በመንግሥት መስሪያ ቤቶችና በግል ተቋማት እጅግ ሥር የሰደደ ሆኗል። እውነታው ይህ ከሆነ ትምህርት ቤቶች ተለይተው እንዴት የመልካም ሥነ-ምግባር

ማእከላት ሊሆኑ ይችላሉ? እነዚህ ተማዎች የፈለቁት እኮ ሳይሰሩ መኖር ተቀባይነት ባገኘበት፣ ሰርቆ በአቋራጭ መበልፀግ እንደ ትክክለኛ አካሄድ በተቆጠረበት፣ ሥልጣን የጥቅም ማስገኛ ምንጭ በሆነበት፣ በወገንና ዘመድ አዝማድ መጠቃቀም ወደ ባህል በተሸጋገረበት፣ እንደደምንም ስልጣን የተቆጣጠረ መሪ ተገፍቶ እሲከወርድ ድረስ መልቀቅ የማይታሰብበት ወዘተ. እየተመለከቱ ናቸው::

ከዚህ ሌላ በሰፈራቸው፣ አልፎ አልፎም በቤታቸው አሉ የሚባሉት ቱባ ባለሥልጣናት ጫት ሲቅሙ፣ ጥንብር ብለው ሲሰክሩ፣ አዳራቸው በየ መጠጥ ቤቱ ሲያደርጉ የሚመለከቱ ወጣቶች «ተከተል አለቃህን እወቅ ዓላማህን» ቢሉ ጥፋቱ የማን ይሆናል? ባቋራጭ መበልፀግ የጊዜው ክስተት በሆነበት ሁኔታ ሳያጠኑ ቆይተው ባቋራጭ ኮርጀው ቢያልፉስ እንዴት በጥፋትነት ሊያዩት ይችላሉ? ስልጣን፣ ሃብት፣ እውቀት በጥረትና በውድድር የሚገኝ መሆኑ ቀርቶ በጉልበት፣ በብልጠትና በቅጥፈት እንደሚገኝ በአካባቢያቸው ሲመለከቱ እነሱስ የትኛውን ይከተሉ?

የአስተማሪው መመዘኛም ባስተማራቸው ተማሪዎች እውቀት፣ ብቃትና ውጤት መሆኑ ቀርቶ ስንት ተማሪዎችን አስመዘገበ ስንቶችስ አለፉ የሚል ከሆነ ለሥነ-ምግባር ለምን ይጨነቃል? እንዲያውም ተማሪዎቹ ኮርጀው በሙሉ ቢያልፉለት የሥራ ዋስትና ይኖረዋል ምስጋናም ያተርፋል:: ኢህአዴግ የሚፈልገው ምን ያህል በአንደኛ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃ ወይም በዩንቨርስቲ እንደተመዘገቡና እንዳለፉ እስከሆነ ድረስ የአስተማሪው የጨዋታ ሕግም ከዚህ የተለየ አይሆንም:: ለሥነ-ምግባር ብልሽት ከሚዳርጉት ምክንያቶች አንዱም ይህ አሠራር ነው ሊባል ይቻላል::

## 6. <u>መምህራንና ችግሮቻቸው</u>

መምህራን ከአጼው ዘመን ጀምሮ በተደራጀ መልክ ብሶታቸውንና ጥያቄዎቻቸውን ሲያቀርቡ ቆይተዋል:: በተለይ በአጼው ዘመን የተቋቋሙ ፓርቲዎች ባለመኖራቸው እንቅስቃሴያቸውን ያለምንም የፓርቲ ጣልቃ ገብነት ሲያካሂዱ ነበር:: ከዘመነ ደርግ ጀምሮ ግን የተለያዩ በጊዜው ያቆጠቆጡ ፓርቲዎች የመምህራን ማኅበርን በቁጥጥር ሥር ሊያውሉት ሲጥሩ ታይተዋል:: በኢህአዴግ ዘመንም ማኅበሩ የገዢው ፓርቲ ተቀፅላ ለማድረግ ብርቱ ጥረት ተደርጓል:: በአሁኑ ጊዜ የኢህአዴግ አባል ያልሆነ መምህር ዋስትና ኖሮት በሥራው የሚቀጥልበት ሁኔታ እጅግ አስቸጋሪ በመሆኑ አብዛኛዎቹ መምህራንና የማኅበሩ አመራር አባላት የኢህአዴግ አባላት ለመሆን ተገደዋል:: ይህ አካሄድ በመሠረቱ የሙያ ማኅበር ዓላማና አደረጃጀት መርህን

ይፃረራል:: የሙያ ማኅበር የሚደራጀው አባላቱ ከመንግሥት የሚደርስባቸውን ተፅእኖ ለማቋቋምና የአባላትን ጥቅም ለማስከበር ነው:: ይህን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ ከመንግሥትና ከፓርቲዎች ተፅእኖ የፀዳ ነፃ ማህበር ሲቋቋም ብቻ ነው::

መምህራን በነፃነት ባልተደራጁበት በአሁኑ ወቅት የኢህአዴግ ፍላጎት ማስፈፀሚያ መሣርያ ከመሆን ሊያመልጡ አይችሉም:: ለዚህ ማስረጃ የሚሆነውም በቅርቡ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር በተደረገው ውይይት ፋይዳ ያለው ውጤት አለመገኘቱ ነው:: አጠቃላይ የመማር ማስተማሩን ሂደት ሊያሻሽሉ የሚችሉ ቀርቶ የመምህራንን ጥቅም የሚያስጠብቁ ጥያቄዎች እንኳ በአግባቡ አልተመለሱም:: የመምህራን ደመወዝ ጭማሪ፣ የቆላ ዓበልና የዝውውር ጥያቄ ቀርበው አጥጋቢ መልስ አልተሰጣቸውም:: በተለይ የመምህራን የደመወዝ ጥያቄ በተመለከተ የተሰጠው መልስ አስቂኝም አሳዛኝም ነው::

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአሁኑ ጊዜ ለመምህራን ደመወዝ ቢጨመር የሚሰጠው ጥቅም አይኖርም በማለት የኢኮኖሚና የገንዘብ ዑደት ሕግጋትን በማጣቀስ ለማስረዳት ሞክረዋል:: ለመምህራን ደመወዝ ቢጨመር የኑሮ ውድነቱን ሊያባብስ እንደሚችል ያለማመንታት ተናግረዋል:: በእርግጥ ኢኮኖሚው ሊሸከመው የማይችል የገንዘብ ዑደት ካለ የዋጋ ንረትን ሊያባብስ ይችላል፤ ሆኖም የመምህራን ደመወዝ ባልተጨመረበት ሁኔታም የዋጋው ንረት እጅጉን ተባብሷል:: በቅርቡ የሚወጡት አሃዞች እንደሚያመለክቱት የዋጋ ግሽበት ባለፈው ዓመት በተመሳሳይ ወቅት ከነበረበት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል :: ይህ ሁኔታ ከመከሰቱ አስቀድሞም ቢሆን መምህራን በሚያገኙት ደመወዝ ብቻ ለመኖር እየቸገራቸው በሌሎች ተጨማሪ ሥራዎች ለመሰማራት ተገደው ነበር:: የኑሮ ውድነቱ በተባባሰበት ሁኔታ ደግሞ ይበልጥ ከመደበኛ ስራቸው ይልቅ ለተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ሥራ ትኩረት እንደሚሰጡ ይገመታል :: ልብ ይበሉ መምህራን ከሙያቸው ውጭ ተጨማሪ ሥራዎችን ለመሥራት በሚገደዱበት ወቅት የተሰማሩበትን ሥራ ለመወጣት ያላቸው ብቃት ያሽቆለቁላል:: ከዚህ የተነሳም የመማር ማስተማሩን ሂደት በእጅጉ ይጐዳል::

የመምህራን ማኅበር ዋና ተግባር የአባላቱን የኑሮ ደረጃ ማስጠበቅና ከተቻለም ማሻሻል እስከሆነ ድረስ በደመወዝ ዙሪያም መደራደር ይኖርበታል:: በሌሎች አገሮች የሙያ የማኅበራት ግምባር ቀደም ተግባር አጠቀላዩን የኑሮ ሁኔታና የዋጋ ግሽበት እየተከታተሉ በደመወዝ ላይ ማስተካከያ እንዲደረግ መታገል ነው:: እንዲያውም የሙያ ማኅበራት የደመወዝ ጭማሪ የሚጠይቁት የዋጋ ግሽበት በሚከሰትበት ወቅት ነው:: ግሽበት በመምህራን ደመወዝ ጭማሪ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የኢኮኖሚው ግለትና

የገንዘብ ዝውውር ዕድገት መጠን ስለሚወሰን የመምህራን ደመወዝ ጭማሪ በማስቀረት ብቻ መቆጣጠር አይቻልም። የዋጋ ንረት ሲኖር ማኅበራት የደመወዝ ማስተካከያ (inflation adjusted income) እንዲደረግላቸው ይጠይቃሉ። ለምሳሌ የዋጋ ግሽበቱ በ10% ካደገ በነበሩበት ሁኔታ ለመቆየት ብቻ የ10% የደመወዝ ጭማሪ ይጠይቃሉ። የዋጋ ግሽበቱ 20% ካደገም እንዲሁ ባሉበት ሁኔታ ለማስቀየት ያን ያህል ማስተካከያ ይደረጋል። ይህ ዓደይነቱ አካሄድ የደመወዝ ማስተካከያ እንጂ የደመወዝ ጭማሪ ተደርጓል አያሰኝም። ደመወዝ ጭማሪ ተደርጓል የሚባለው ከግሽበቱ መጠን ያለፈ የደመወዝ ጭማሪ ሲደረግ ብቻ ነው። በመሆኑም ግሽበት ባለበት ሁኔታ የመምህራን ደመወዝ የማይስተካከል  ከሆነ በተጨባጭ ደመወዛቸው ቀንሷል ይባላል። ይህ የሚሆነውም በተመሳሳይ ደመወዝ ድሮ ይገዙት ከነበረው ሸቀጥና ያገኙት ከነበረው አገልግሎት ያነሰ ስለሚያገኙ ነው።  ነገሩ መታየት የነበረበት ከዚህ አንፃር ሲሆን ጠ/ሚኒስትሩ ግን የመምህራን ደመወዝ ቢጨመር ግሽበትን አስከትሎ የመምህሩ የኑሮ ደረጃ ሊጎዳ ይችላል በሚል እውነታውን በሚድበሰብስ መንገድ አልፈውታል።

የመምህራን የመጠለያ ችግርም በተመሳሳይ መንገድ መልስ ሰጥተውበታል። በክልሎች መምህራን ተደራጅተው ቢቀርቡ የኮንዶምንየም ቤቶች ሊያገኙ እንደሚችሉ ገልፀውላቸዋል። ይህን እየተናገሩ ያሉት በክልሎች ኮንዶሚንየም ቤት ከዝቅተኛው ደመወዝተኛና የግል ተዳዳሪ አቅም በላይ በመሆኑ ገዢ አጥቶ እንደቆመ አጥተውት አይመስለኝም። ኑሮው ከእጅ ወደ አፍ የሆነው መምህር ቀርቶ ከሱ የተሻለ ገቢ ያላቸው ዜጎች እንኳ በክልሎች የኮንዶሚንየም ቤት ባለቤት መሆን ተቸግረዋል። የዚህ ዓይነት መልስ ተገቢ ካለመሆኑም በተጨማሪ መምህራን ያነሱትን የኑሮ ችግር የሚያድበሰብስ ነው። በመሆኑም መምህራን ወኔያቸው ይቀዘቅዛና የማስተማር ፍላጎታቸው ይዳከማል ወይም ደግሞ እንደሚታየው ሥራቸውን እየለቀቁ በሌሎች ሙያዎች ይሰማራሉ። በዕንቅርተ ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ጥራት ያለው ትምህርት መስጠት ቀርቶ ባለበት ለማስቀጠልም አስቸጋሪ ይሆናል ። አሉታዊ ተጽእኖውም ለትምህርቱ ዘርፍ ብቻ ሳይሆን ለአጠቃላዩ የአገር እድገት ይሆናል።

## 7. የመጨረሻ ውጤቱ

እንግዲህ በአገራችን ስላለው የትምህርት ጥራት፣ ብቃትና ውጤት እንዲሁም ስለተማሪዎች ስነ-ምግባርና ሌሎች ጉዳዮች በእርግጠኝነት መናገር ካስፈለገ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ማገናዘብ ተገቢ ይሆናል። በአገራችን የትምህርት ዘርፉ ከላይ በተጠ

ቀሱት ችግሮች የተተበተበ ነው። ከሞላ ጎደል ከዚህ ችግር ነፃ ናቸው ሊባሉ የሚችሉት ሊሂቃን ተማሪዎችን በማፍራት የተሰማሩት የተወሰኑ ትምህርት ቤቶች ናቸው። የትምህርት ዘርፉ ተበላሽቷል በማለት ሙሾ የሚያወርዱት አብዛኞቹ ባለስልጣናት ልጆቻቸውን የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እንዲቀስሙ የሚልኳቸው ወደነዚህ የሊሀቃን ትምህርት ቤቶች ነው። አንዳንዶቹም ልጆቻቸውን ከደመወዛቸው በላይ በሚከፈልባቸው ትምህርት ቤቶች ይልካሉ። ያን ያህል ገንዘብ ለመክፈል እንዴት እንደቻሉ ለጊዜው ወደ ጐን ትተን ልጆቻቸው ቢያንስ አሉ በተባሉት ትምህርት ቤቶች እያስተማሩ ነው። የሁለተኛ ደረጃ እንዳጠናቀቁም ያለ ምንም ችግር በውጭ አገር ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ይደረጋል። የሥነ-ምግባር ጉድለት ካልጠለፋቸው በስተቀር የተጠቀሱት ችግሮች እነሱን አይመለከቱም። ታዲያ የችግሩ አካል ባልሆኑበት ትምህርት ዝብርቅርቁን ቢወጣና ቢዘቅጥስ ምን ቸገራቸው። የችግሩ ቀጥተኛ ሰለባ ስለማይሆኑ ደንታ አይኖራቸውም። እንዲሁ የአዞ እንባቸውን ብቻ ያወርዳሉ።

የትምህርት ሥርዓቱ ቀጥተኛ ሰለባዎች በሚልዮኖች የሚቆጠሩ በከተማና በገጠር የሚገኙ ተማሪዎች ናቸው። ትምህርቱ ከጥራት፣ ከብቃትና ውጤታማነት አንፃር ከፍተኛ ችግር ስላለበት እንዲሁ ሲገቡና ሲወጡ ይቆጠራሉ እንጂ ትምህርታቸውን በተሳካና በሚፈለገው ጨርሰው በራስ የሚተማመኑበት ሁኔታ የለም። በርካታዎቹ ለሥራ አጥነትና ተስፋ መቁረጥ ይዳረጋሉ። ሥራ ያጣና ተስፋ የቆረጠ ወጣት ደግሞ የተለያዩ መጥፎ ስነ-ምግባሮች ሰለባ ይሆናል። በአገራችን ከትምህርት ጋር በተያያዘ እየተከሰተ ያለው አንዱ ችግርም ይኸው ነው።

ከዚህ ሌላ ትምህርት ቤቶች የፀጥታ ስጋት መሆናቸው አልቀረም። ይኸ ስጋት ደግሞ ገዢው ፓርቲ ቁጥጥሩን እንዲያጠናክር አስገድዶታል። ከዚህ የተነሳም ጠቅላላ በትምህርት የተሰማራውን ማኅበረሰብ የድርጅት አባል በማድረግ ሊቆጣጠረው ይሞክራል። ከተቻለ ሁሉንም መምህራንና አብዛኛውን ተማሪ የኢህአዴግ አባል ለማድረግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው። ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሳይቀር የትምህርት ተቋማት መሆናቸው ቀርቶ የፓርቲ ተቋማት እስኪመስሉ ድረስ በአባላት ተጥለቅልቀዋል። ለአካዳሚ ጥራትና ብቃት ተብሎ ከሚደረገው ውይይትና ስብሰባ ይልቅ የፓርቲ አባላት ስብሰባዎችና ውይይቶች ተበራክተዋል። የአካዳሚ ነፃነት ደብዛው ጠፍቶ የአንድ ፓርቲ የበላይነት በተቋማቱ ነግሷል። ገና ለጋ ህፃናት በሆኑት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያለው ሁኔታም ተመሳሳይ ነው።

በአገራችን የትምህርት ጥራት፣ ብቃትና ውጤታማነት እንዳይኖር የፈረደበት ገዢው ፓርቲ ራሱ ነው። የሙያ ነፃነትን በፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ተክቶ ትምህርትንና

የትምህርት ተቋማትን በፖለቲካ መሳሪያነት እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡ ታዲያ ራሱ ገድሎ ራሱ ሙሾ ቢያወርድ እንዴት መፍትሄ ሊገኝ ይችላል? በትምህርት ዙሪያ የሚነሡትን ችግሮች በመቅረፍ ረገድ ሊረዱ የሚቸሉትን ሙሁራን የአካዳሚ ነጻነት ነፈጎና አስወግዶ በፓርቲ አባላት ሊመራው ቢሞክር እንዴት ውጤት ሊገኝ ይችላል፡፡ የሚታጨደው የተዘራው ነውና ትምህርታችን ዘወትር ጥራት፣ ብቃትና ቅልጥፍና ሳናስመዘግብ እያለቅስን እንኖራለን፡፡